# የ2007 የፀሎት ርዕሶች (የዐርብ የፀሎት አገልግሎት እና የ24 ሰዓት የጸሎት አገልግሎት)

*1. ኢትዮጵያ/አዲስ አበባ*

- የኤይድስ በሽታ በሀገሪቱ በፍጥነት እየተዛመተ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ
  1.2 ሚሊዮን ልጆች በበሽታው እናትና አባታቸውን አጥተዋል።
- በዓለም ድሆች ከሚባሉት አንዷ ናት
- የሕዝብ ብዛት 73,053,286 ሲሆን
- ሀይማኖት፤
  ጠቅላላ ክርስቲያን - 65 %
  እስልምና - 21 %
  ሌሎች - 14 %

*የሚፀለይባቸው ርዕሶች፤*

1.1. የጣዖት አምልኮ፤ ጥንቆላና የአጋንንት ሥራ ሁሉ እንዲፈራርስ በኤሊያስ ጥያቄ በበዓል ነብያት ላይ የወረደው እሳት በኢትዮጵያም እንዲወርድና ጣዖታትን እንዲበላ አንፀልይ
1.2. መሬቷ እንድትፈወስ እና በረሃብ ምክንያት ስለ ሚሰደዱት ልጆችና ቤተሰቦች እግዚአብሔር ይህንን ጠባሳ እንዲፈውስ አንፀልይ (መዝ. 103፡35)
1.3. በረሃቡ የተጎዱ እንዲቋቋሙ የሚፈለገውም ዕርዳት ከለጋሽ አገሮች በወቅቱ እንዲደርስ አንፀልይ
1.4. የመሪዎችን ልብ ወደ ሕዝቡ የሕዝቡን ልብ ወደ መሪዎች እንዲሆንና የፖለቲካው ቀውስ እንዲፈወስ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ረዳቶች በእግዚአብሔር ምሪት፤ ምክርና ጥበብ ሕዝቡን ለማገልገል ልባቸው እንዲቀልጥ አንፀልይ

2. ኤርትራ

- የሕዝብ ብዛት **4,567,999**
- ሀይማኖት
  ጠቅላላ ክርስቲያን - 48 %
  እስልምና - 47 %
  ሌሎች - 5 %

2.1. 75 ሺህ ያህል በውጭ አገር የሚኖሩ ኤርትራውያን ወደ ክርስቶስ እንዲመጡና ወደ አገራቸው ወንጌልን በማሰራጨት እንዲያገለግሉ መጸለይ
2.2. በርካታ ፓስተሮች (አገልጋዮች) እና ምዕመናን በእስርና በእንግልት ላይ በአገሪቱ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ስለአሉ በዚህ ጉዳይ ላይ መጸለይ
2.3. ለክርስቲያን ሠራተኞች የተዘጋው በር እንዲከፈት፤ የእስልምና ሀይማኖት አክራሪነት መንፈስ እንዲመታ መጸለይ
2.4. ወንጌል እንዲሰበክ፤ የእግዚአብሔር ክብር ወደ አገሪቱ እንዲመጣ፤ ጸረ ክርስቶስ መንፈስ እንዲመታ፤ እንዲሁም መሪዎች እግዚአብሔርን በመፍራት ሕዝባቸውን እንዲመሩ መጸለይ

3. ፓስተር እንድሪያስ፤
   ቤተሰቡንና አገልግሎቱን በተመለከተ መጸለይ
4. የቤተክርስቲያናችን መንፈሳዊ አባት ለሆነው ፓስተር ዳንኤል
   ቤተሰቡንና አገልግሎቱን በተመለከተ መጸለይ

5. በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ላሉት ፕሮግራሞች በሙሉ፤
   5.1. የሕፃናት ፕሮግራም አገልግሎት - ለሕፃናት፤ ለአስተማሪዎችና ለቤተሰብ
   5.2. የቤተክርስቲያን ሕንፃ ሥራ አገልግሎት
   5.3. የወጣቶች ፕሮግራም
   5.4. የአስተናጋጆችና ዲያቆናት አገልግሎት
   5.5. የጽዳት አገልግሎት
   5.6. የቤተሰብ አገልግሎት
   5.7 የአርብ የፀሎት ጓዶች አገልግሎት
   5.8. የቤተክርስቲያናችን የዕሮብ፤ የአርብና የዕሑድ ፕሮግራሞች
   5.9. የዝማሬ አገልግሎት
   5.10. የካሴት አገልግሎት
   5.11. ለአጋፔ የሕጻናት ማሳደጊያ ስኬትና አገልግሎቱ እንዲሰፋ
   5.12. የእህቶች አገልግሎት
   5.13. የወብ ሳይት (Website) አገልግሎት
   5.14. የሬዲዮ አገልግሎት
   5.15. የ24 ሰዓት የጸሎት አገልግሎት
   5.16. የቪዲዮ አገልግሎት

በነዚህ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ላይ የእግዚአብሔር ሞገስ፤ ቅባትና የመንፈስ ቅዱስ ፀጋዎች እንዲበዙ እንጸልይ

6. የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በሚኔሶታ እና ኢትዮጵያን ልጆችን ከኢትዮጵያ በማምጣት (adoption) ከሚያሳድጉ በከተማችንና አካባቢው የሚኖሩ አሜሪካውያን ቤተሰቦች ጋር ስለሚደረግ ትብብርና የአማርኛ ቋንቋ ጥናት መጸለይ

7. በቤተክርስቲያናችን የተጀመረው የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ (Revival) እንዲቀጥል እንጸልይ

8. በመካከለኛው ምሥራቅ ስለ አለው ችግር፤
   ለእስራኤል፤ ለኢራቅ፤ ለሊባኖስና ለፍልስጤማውያን እንጸልይ

9. ለአሜሪካና ለዓለም በሙሉ እንጸልይ

10. በአጠቃላይ በዓለም ላይ ለሚድኑ አዳዲስ ነፍሳት እንጸልይ

11. ለክርስቶስ አካል በአጠቃላይ እንጸልይ

*(ሐዋ. 4፡30÷31)*